# የብርቱካን ሚደቅሳ እንደገና መታሠር በአገራችን እየታየ ያለውን የሕግ ጥሰት አጉልቶ ያሳያል!

# ከሕግ በላይ መሆን ይቁም!

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሣ «ሕገ-መንግሥቱንና  ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመለወጥ ሙከራ አድርገዋል» በማለት በተከሰሱበት ጉዳይ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ፕሬዚደንት ሐምሌ 12 ቀን 1998 ዓ.ም የተፃፈ ደብዳቤ ሙሉ ይቅርታ የተሰጣቸው መሆኑን» ያረጋግጣል፡፡

ወ/ት ብርቱካን ለወደፊቱ በእንደዚህ ዓይነት ተግባር እስካልተሳተፉና ሕገ-መንግሥቱን የማክበርና የማስከበር ዜግነታዊ ግዴታቸውን በአግባቡ እስከተወጡና በሕገ-መንግሥቱ የተደራጁ የመንግሥት ተቋማትን  ሥልጣንና ተግባር ተቀብለውና አክብረው እስከቀጠሉ ድረስ ሙሉ ይቅርታው ፀንቶ እንደሚቆይ ፕሬዚዴንቱ የሰጡት የይቅርታ ሰርተፊኬት የረጋግጣል፡፡ ወ/ት ብርቱካን ይህንን የገቡትን ቅድመ ግዴታ በምንም መልኩ ያልጣሱ ሲሆን የገቡትን ግዴታ ጥሰዋል የሚል በመንግሥት የቀረበ ክስም የለም፡፡

አዋጅ ቁጥር 395/1996 አንቀጽ 16 ይቅርታ የሚሰጥባቸው ሁኔታዎችን ይዘረዝራል ከእነዚህም ውስጥ:-

ሀ/ የይቅርታው ውሳኔ ለይቅርታ ተቀባዩ ከደረሰ በኋላ የይቅርታው ውሳኔ በማጭበርበር ወይንም በማታለል የተገኘ መሆኑ ከተረጋገጠ ይቅርታው ሊሰረዝ እንደሚችል ተደንግጎአል፡፡

ለ/ ይቅርታ የተሰጠው በቅድመ ሁኔታ የተሰጠ ሆኖ ቅድመ ሁኔታው ከተጣሰ ይቅርታው ሊሰረዝ እንደሚችል ሕጉ ይገልፃል፡፡

ለወ/ት ብርቱካን ተሰጥቶ የነበረው ይቅርታ የተነሣው መንግሥት በብዙሃን መገናኛ እንደ ገለፀው ከሆነ በአንድ መድረክ ላይ  ይቅርታ አልጠየቅኩም ብላዋል በሚል ነው፡፡ ይኸ ደግሞ በምንም መልኩ ይቅርታን ሊያሰርዝ የሚችል ድርጊት ነው ሊባል አይችልም፡፡  ይህም ሆኖ ለወ/ት ብርቱካን ተሰጥቶ የነበረው ይቅርታ ሲሰረዝ መሟላት የነበረባቸው ሕጉ የሚደነግጋቸው ሥነ- ሥርዓቶች ሙሉ በሙሉ ተጥሰዋል፡፡

አዋጅ ቁጥር 395/1996 አንቀጽ 17 በሚደነግገው መሠረት ይቅርታ ለማሰረዝ የሚያበቃ በቂ ምክንያት ሲገኝ ምክንያቱ በግልጽ በጽሁፍ ተዘጋጅቶ ለይቅር ተባዩ እንዲደርሰው መደረግ አለበት፡፡ ሆኖም ወ/ት ብርቱካን ይቅርታው መሠረዙ ሕጉ በሚያዘው መሠረት በጽሁፍ ሳይደርሳቸው፤ ይቅርታው መሠረዝ እንደማይገባው፤ መልስ ለመስጠት የሃያ ቀናት ጊዜ የመሰጠት መብታቸው ሳይከበር ሰብአዊ መብታቸውን በሚጥስ መልኩ ወደ ወህኒ ቤት ተወስደዋል፡፡

ስለዚህ ወ/ት ብርቱካን ይቅርታ ሲሰጣቸው የገቡትን ግዴታ ያልጣሱ በመሆኑ የተሰጣቸው ይቅርታም የተሰረዘው ሕጉ የሚደነግገውን ሥርዓት በጣስ መልኩ በመሆኑ፤ ይቅርታው ተሰርዞ ወደ ወህኒ በወረዱበት ወቅት የደረሰባቸው እንግልት በሕገ-መንግሥቱ የተከበረላቸው ሰብአዊ መብቶችን የሚጥስ በመሆኑ፤ የተሰረዘው ይቅርታ ውድቅ ሆኖ ቀደም ሲል የተሰጣቸው ይቅርታ መጽናት እንዳለበት ሕጉ የግድ ይላል::

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሣ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) ሊቀመንበር በመሆናቸው ይህ ሕገወጥ ድርጊት የፓርቲውን እንቅስቃሴ ለማደናቀፍ ታልሞ የተፈፀመ ድርጊት ነው የሚል እምነት በፓርቲው ዘንድ አሣድሯል::

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሣ ታህሣሥ 20 ቀን 2001 ዓም ከቀኑ በ 8:00 ሰዓት ላይ ማንነታቸውን ባላሳወቁና ህጋዊ መጥሪያ ባላሳዩ ግለሠቦች እንግልትና ወከባ ደርሶባቸዋል:: በወቅቱም አብረዋቸው በነበሩት በፐ/ር መስፍን ወ/ማሪያምና የወት/ብርቱካን ሾፌር በሆኑት አቶ አብዱረህማን አህመድ ላይ የድብደባ ድርጊት ተፈጽሞባቸዋል:: ከላይ የተጠቀሱት ህገ-ወጥ ድርጊቶች የሚያመለክቱት የህግ የበላይነት መጣሱን ብቻ ሣይሆን የዜጎችን ሠብአዊና ሕገ-መንግሥታዊ መብቶቻቸው መረገጣቸውን ነው::

በመሆኑም መንግሥት በአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር ላይ የወሰደው ሕግን ያልተከተለ እርምጃ ከግለሰቧ አልፎ በፓርቲያችን ላይ ያነጣጠረ መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ ልብ ሊለው ይገባል:: ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሣ የአንድነት ፓርቲ ሙሉ ድጋፍ ያላቸውና የድርጅቱ ሊቀመንበር መሆናቸውን ፓርቲው በአጽንኦት እየገለፀ ከጎናቸው የቆመ መሆኑን ያረጋግጣል::

በተጨማሪም የወ/ት ብርቱካንን መታሠር አስመልክቶ አውራምባ ታይምስ ጋዜጣ በ21/4/2001 በወጣው እትሙ ዶ/ር ኃይሉ አርአያን በመጥቀስ «ይህ የወ/ት ብርቱካን የግል ጉዳይ እንደሆነና እርሳቸውን ብቻ እንደሚመለከት ተገልፆልናል» በሚል የቀረበው ሪፖርት ከእውነት የራቀና የፓርቲውን አቋም የማይወክል መሆኑን በአጽንኦት እንገልፃለን::

የኢትዮጵያ ህዝብም ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሣን አስመልክቶ ከተወሰደው እርምጃ በስተጀርባ ያለውን ሁኔታ በማጤን በሀገራችን ዴሞክራሲንና የህግ የበላይነትን ለማስፈን የሚደረገውን ሠላማዊና ህጋዊ ትግል በይበልጥ እንዲያጠናክር አንድነት ፓርቲ ጥሪውን ያቀርባል:: ለሠላማዊ ትግል መጎልበት፤ ለዜጎች ሠብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት መከበር እንዲሁም ለህግ የበላይነት መረጋገጥ የቆሙ መንግሥታትና ድርጅቶችም የትግላችን አጋዥ እንዲሆኑ ጥሪያችንን እናቀርባለን::

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)
ታህሣሥ 21/04/2001 ዓም
<u>አዲስ አበባ</u>